# ግጭትን ሚራገብ ተጠያቂነትን ያስከትላል!

ታዬ ከበደ 10-04-17

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ሰሞኑን በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሶማሌ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተውን ሁከት አስመልክተው በችግሩ ወስጥ ተሳትፈው ግጭቱን ለሚራገብ የሚሞክሩ የውጭም ይሁን የወስጥ ሃይሎችን ጠንከር ያለ ማስጠንቀቂያ እንደሰጧቸው ይታወሳል፡፡

ምንም እንኳን ከእርሳቸው ማስጠንቀቂያ በኋላ ችግሩ የቀዘቀዘ ቢሆንም፤ አሁንም በተለያዩ ዘወጎች ግጭትን በሚራገብ ስራ ላይ የተጠመዱ አካላት ሊኖሩ እንደሚችሉ እሙን ነው፡፡ እነዚህ ሃይሎች የህዝቦች ፍላጎት ያልሆነውን ግጭት ሚራገባቸው ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው ማንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የምትከተለው ስርዓት ግጭትን የሚያርቅ እንጂ ለግጭት የሚጋብዝ ስላልሆነ ነው፡፡

እርግጥ ግጭቶች በየትኛውም ሁኔታ ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ግጭት ሚፈጠር የለበትም ሊባል አይችልም፡፡ በየትኛውም ማህበረሰብ ማስተጋብራዊ ግንኙነት ወስጥ ግጭት ሚፈጠሩ አይቀርም፡፡ ዋናው ጉዳይ እንዴት አድርገን ልናረጋጋቸው እንችላለን የሚለው ነው፡፡ ግጭቶች በራሳቸው መጥፎ አይደሉም፡፡ መጥፎ የሚያደርጋቸው አስተሳሰባችን ነው፡፡

ለወጥን ማስረት ባደረገ አስተሳሰብ ከተቃኘ፣ ግጭት የለወጥ ማሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ፌዴራሊዝም የግጭት ማሻ ነው የሚባለው አማካከት ማስረት የሌለው ነው፡፡ ኢትዮጵያ የምትከተለው ፌዴራላዊ ስርዓት ማቻቻልን ያመጣ በሂደትም በማልበት ላይ ያለ ነው፡፡ ምክንያቱም የስርዓቱ አወቃቀር ብዝሃነትን እንደ ወበት አድርጎ የሚሳ በመሆኑ ነው፡፡ በልዩነት ወስጥ ያለ አንድነትን በማጠናከር የማቻቻል መንፈስ እንዲዳብር ተደርጎ በህዝቦች ስለተዋቀረ ነው፡፡ በመሆኑም እዚህ አገር ወስጥ ለግጭት የሚሆን ስፍራ እንደሌለ ግጭት አራጋቢዎቹ ሊያወቁት ይገባል፡፡

ያም ሆኖ ግጭትን የሚያራግቡ ሃይሎች ለልማት በመትጋት ላይ በሚገኘው ወጣት እጅ እሳት ለሚጨበጥ በበሞከር ከስሮ የወደቀ ፖለቲካቸውን ለማንሰራራት የሚከጅሉትን ፀረ-ሰላም ሃይሎችን ማንነት በሚባ የሚያወቀው ዕወነታ ነወኖ።

ስለሆነም ህዝቡ በሂደት እንደ አሜኬላ እሾህ ከማሉ እየነቀለ በሚወጣት ህግ ፊት እንደሚያቀርባቸው በእርግጠኝነት መግለጽ ይቻላል። ምክንያቱም በሀገር አቀፍ ደረጃም ይሁን በክልሉ እየተማዘገበ ካለው ባለ ሁለት አሃዝ ፈጣንና ተከታታይ ልማታዊ ዕድገት ተጠቃሚነቱ እንዲስተጓጎልበት ስለሚፈልግ ነው።

በሙሆኑም በአሸባሪዎችና በፀረ-ሰላም ሃይሎች አሉባልታ እንደ ቦይ ወሃ የሚ ዳ ህዝብም ሆነ መንግስት አለመኖሩን ማወቅ የሚገባ ይመስለኛል። እርግጥ የፀረ-ሰላም ኃይሎቹ አሉባልታ የሰላም ወዳዱና ከሌሎች የሀገሪቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጋር በአንድነት የሚጸግ ፍላጎት ያለው የኦሮሞም ይሁን የኢትዮጵያ ሶማሌ ህዝብ አጀንዳ አይደለም።

የሁለቱ ህዝቦች ፍላጎት ከሌሎች የሀገሪቱ ህዝቦች ጋር በመተሳሰብና በመደጋገፍ በጋራ የሚልማት፣ ከአጎራባች ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ጋር በፍትሐዊ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲሁም ባደረገው መራር ትግል ዕወን እንዲሆን ባስቻለው ህገ-መንግስት ላይ የሰፈሩት መብቶቹ ሳይሸራረፉ እንዲተገበሩላቸው ነው።

በግጭት አራጋቢዎች አሉባልታ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ፤ ሴራው ሆን ተብሎ ሁለቱ ህዝቦች አገራዊና ክልላዊ ተጠቃሚነት ለማዳናቀፍ እንዲሁም በትግል ያገኛቸውንና እያጎለበታቸው የሚገኙትን ሁለንተናዊ ህገ-መንግስታዊ መብቶቹን ለመሸርሸር ብሎም ህዝቡ ተረጋግቶ በልማት ስራው ላይ እንዳያተኩር ለማድረግ የታለመ ነው።

እንደሚታወቀው ሁሉ የኦሮሞና የኢትዮጵያ ሶማሌ ህዝቦች ባለፉት ዓመታት በተጎናጸፏቸው የልማትና የዕድገት ዕድሎች በብቃት በመጠቀም ከፍተኛ ለወጥ ማስመዝገብ ችለዋል፡፡ በህዝቦች ይሁንታ የተመሰረተው ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በህዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ ማንባት ከጀሚበት ወዲህ በሁለተም እየታየ ያለው ለወጥ ከፍተኛ ነው፡፡

ከለወጦቹ መካከል በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን በተመዘገቡ ለወጦች አጠቃላይ የሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት በሁለት አኃዝ እንዲያድግ አስችሏል፡፡ በዚህ ሂደት ወስጥ የህዝቡ ቀጥተኛ ተሳታፊነትና ባለቤትነት ነበር። ያለ ህዝቡ ይሁንታና ፈቃድ የተከናወነ ነገር የለም፤ ወደፊትም አይኖርም።

ሆኖም የፖለቲካ ኪሳራ የደረሰባቸው ግጭት አራጋቢዎች ሁሌም በክልሉ ላይ በማተኮርና በሽብርተኝነት ከተፈረጁ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀትና በጸረ ሰላም ሚዲያዎች የሀሰት ወሬ በመንዛት ሁከት ለመፍጠር እየሞከሩ ነው። የሚሳካለቸው ግን አይደለም።

እነዚህ ግጭት አራጋቢዎች ቀደም ባሉት ጊዜያት በፈጠሩት እኩይ ሴራ አንድም ስንዝር መራመድ ያቃታቸው ናቸው። በዘመናት የትስስር ድር የተጋመዱት የሁለቱ ክልል ህዝቦች የአእምሮ ዕድገትና የፈጠራ ክህሎት እንዳይዳብር፣ ተወዳዳሪነታቸው እንዲደናቀፍና ድህነትና ኋላቀርነት በክልሉ ስር ሰዶ እንዲቆይ ያላቸውን ከፉ ምኞት ለመተግበር ጥረት ሲያደርጉ አድርገዋል። ሊሳካላቸው ባይችልም።

እንደ እውነቱ ከሆነ የሁለቱ ክልል ህዝቦች በተፈጥሮ በተቸራቸው ቋንቋ የማጠቀም መብታቸው ለዘመናት ተነፍጎ ከኖረበት ሁኔታ ራሳቸውን በማላቀቅ ዛሬ ላይ ቋንቋቸው የሳይንስ፣ የጥናትና ምርምር እንዲሁም የእድገት ምንጭ በመሆን ከፍተኛ ለውጥ እያስመዘገበ ይገኛል፡፡ ከሌሎች የሀገራችን ህዝቦች ጋር በመሆንም ባካሄዱት መራርና እልህ አስጨራሽ ትግል ዘርፈ ብዙ ለውጦችን በማምጣት የየክልላቸውን ህዝቦች በየደረጃው ተጠቃሚ ማድረግ ችለዋል።

ይህ በክልሎቹ እየተመዘገበ ያለው ዕድገት የሚያሳበዳቸው እነዚህ ግጭት አራጋቢዎች የልማቱን ግስጋሴ ባዩ የጥፋትና የብተና አቋሞቻቸው ከመቃብር በታች ይወሉብናል በሚል ስጋት የሞት ሽረት ትግል ማድረጋቸው የማይቀር ቢሆንም፤ የሁለቱም ክልል ህዝቦች የእነዚህን እኩይ ሃይሎች ትክክለኛ ፍላጎት በማንዘብ ሴራቸውን ዛሬም እንደ ትናንቱ ሊያመክኑት ይገባል።

ግጭት አራጋቢዎች የህዝቡ ፍላጎት ያልሆነን አጀንዳ በማዛዝ በሁለቱም ክልሎ ወስጥ የሰው ህይወት እንዲጠፋና ንብረት እንዲወድም አድርገዋል። አንዳንደም የገቢ የሆኑ የህዝቦችን ጥያቄዎች ከማጠን በላይ በማክንና ለግጭት መንስኤ እንዲሆን በማድረግ እኩይ ሴራቸውን ሲያከናወኑ ተስተወለዋል። ያም ሆኖ ግጭትን ማራገብ ተጠያቂ እንደሚያደርግ እነዚህ ሃይሎች ሊገነዘቡ ይገባል።

የአገራችን ፌደራላዊ ስርዓት የህግ የበላይነት የነገሰበት በመሆኑ የትኛውም አካል ግጭትን በማራገብ ተግባር ላይ ተሳትፎ እስከተገኘ ድረስ ከተጠያቂነት አያመልጥም። በመሆኑም በውጭም ይሁን በወስጥ የሚገኙ ግጭት አቀጣጣዩች ተግባራቸው መልሶ ራሳቸውን እንደሚያስጠይቃቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል።